# HR2003 በተመለከተ ያሉ ግራ መጋባቶች
# የዲፕሎማሲዉን እንቅስቃሴ በተመለከተ አስተያየት

አማኑኤል ዘሰላም
work_amanuel@yahoo.com

August 13 2008

በቅድሚያ HR2003 በተመለከተ ሃሳብ ከመወርወሬ በፊት በአጭሩ የአሜሪካንን የመንግስት መዋቅር በአጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁኝ።

## የአሜሪካ መንግስት መዋቅር

የአሜሪካ የበላይ ሕግ፣ ሕገ መንግስቱ ነዉ። ሕገ መንግስቱ በዉስጡ ሰባት አንቀጾችና 27 ማሻሻያዎች (amendments) አሉት። በሌሎች አገሮች እንዳሉ ሕገ መንግስቶች ሁሉ የአሜሪካን ሕገ መንስግትም በየጊዜዉ ሊሻሻል ወይንም ሕገ መንግስቱን ባልተጻረ መልኩ የተለያዩ ሕጎች ሊወጡ ይችላሉ።

በአሜሪካ ሶስት የመንግስት አካላት አሉ። እነርሱም ሕግ አዉጪዉ፣ ሕገ አስፈጻሚዉና ሕግ ተርጓሚዉ ናቸዉ። (executive, legislative and judiciary branches)

የሕገ አስፈጻሚ አካል (executive branch)ካቢኔዎቹን፣ የጦር ኃይሉን፣ በየአገሩ ያሉ ኤምባሲዎችን የመሳሰሉት ሁሉ የሚያንቀሰቀስ፣ አሁን ባለዉ ሕግ መሰረት፣ ሕግና ሥርዓት የሚያስጠብቅ ፣ ለዜጎችም የሚያስፈልጉ መሰረታዊ አገልግሎቶች የሚሰጥ አካል ነዉ። ይህን አካል የሚመራዉ በአራት አመት በቀጥታ በሕዝብ በሚመረጥ የአገሪቱ ፕሬዘዳንት ነው።

ኮንግረስ ተብሎ የሚታወቀዉ የሕግ አዉጪዉ አካል (legislative branch) ሁለት የተለያዩ አካላት አሉት። እነርሱም ሴኔትና የሕዝብ ምክር ቤት ናቸዉ። ሴኔት በአሜሪካ ያሉ ስቴቶችን( ክፍለ አገራት) የሚወክል ሲሆን የሕዝብ ምክር ቤት ደግሞ ሕዝብን በቀጥታ የሚወክል ነዉ። በሴኔት ከያንዳንዱ ስቴቶች ሁለት ሁለት ሴኔተሮች ሲኖሩ ባጠቃላይ መቶ ይደርሳሉ። በሕዝብ ምክር ቤት ዉስጥ 435 የምክር ቤት አባላት አሉ። የሕዝብ ምክር ቤት አባላት በየሁለት አመቱ ሲመረጡ፣ ሴኔትሮች ደግሞ በየስድስት አመት ይመረጣሉ። (አሁን ለፕሬዘዳንትነት የሚወዳደሩት ባራክ ኦባማና ጆን ማክኔ ሁለቱም ሴኔቴሮች ናቸዉ)

ሕገ አተርጓሚዉ አካል (judiciary branch) ፣ ዜጎች የሕግ ዉዝግብ ሲኖራቸዉ የአገሪቱን ሕግ ተመልክቶ እልባት የሚሰጥ አካል ነዉ። አሜሪካንን በሙሉ የሚሸፍኑ አሥራ አንድ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች አሉ። ለምሳሌ ኢሊኖይ፣ ኢንዲያናና ዊስኮንሲንን የሚያገልግለዉ የሰባተኛዉ ፌዴራል ፍርድ ቤት ነው። ከነዚህ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች በላይ ደግሞ 9 አባላት ያሉት የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት አለ። እነዚህ ዳኞች በፕሬዘዳንቱ ተመርጠዉ በሴኔት የጸደቁ ሲሆኑ ስራቸዉ ግን ሙሉ ለሙሉ ከሌሎቹ የመንግስት አካለት ነጻ የሆነና የጊዜ ገደብ የሌለዉ ነዉ።

## የሕግ ማዉጣት ሂደት

አንድ ሕግ ሲወጣ መጀመሪያ በሴኔት ወይንም በሕዝብ ምክር ቤት ዉስጥ መቅረብ አለበት። ሁለቱም የሕግ አዉጪ አካላት ሕግን ለማዉጣት የሚጠቀሙበት የራሳቸዉ የሆነ አሰራር አላቸዉ። ሁለቱም ለተለያዩ ጉዳዮች የተለያዩ ኮሚቴዎችን አዋቅረዉ ይንቀሳቀሳሉ። ለምሳሌ የዉጭ ግንኙነትን በተመለከተ የራሱ ኮሚቴ አለ። የመከላከያን ፣ የባጀትን በተመለከተ እንደዚሁ። እያንዳንዱ ኮሚቴ ደግሞ በዉስጡ የተለያዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች

አሉት። ለምሳሌ በዉጭ ግንኙነት ኮሚቴ ዉስጥ የአፍሪካ ጉዳይ ፣ የመካከለኛዉ ምስራቅ ጉዳይ ...የተባሉ የተለያዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች አሉ።

ብዙ ጊዜ ሕግ ሲወጣ ያንን ሕግ የሚመለከተዉ ንኡስ ኮሚቴ ነዉ ሂደቱን የሚጀምረዉ። ለምሳሌ HR2003 መጀመሪያ እንዲቀርብ ያደረገዉ በዶናልድ ፔንና ክሪስ ስሚዝ የሚመራዉ የአፍሪካ ጉዳይ ንኡስ ኮሚቴ ነበር። ያ ንኡስ ኮሚቴ ካሳለፈዉ በኋላ ለውጭ ግንኙነት ሙሉ ኮሚቴ ቀርቦ እንዲያልፍ ተደረገ። ከዚያም በመላዉ የሕዝብ ምክር ቤት ሊጸድቅ ቻለ።

አንዳንድ ረቂቅ ሕጎች በጣም አስቸካይ ከሆኑ፣ ንኡስ ኮሚቴዉን አልፎ የሙሉ ኮሚቴ ሰብሳቢ ረቂቅ ሕግ ለዉይይት ሊያቀርበዉ ይችላል። ካስፈለገም ደግሞ የምክር ቤቱ ቃላቀባይዋ ፋስት ትራክ በሚሉት አሰራር በቀጥታ አንድን ረቂቅ ሕገ ሙሉ ምክር ቤቱ እንዲወስንበት ለዉይይትና ለድምጽ አሰጣጥ ማቅረብ ትችላለች። አንድ ሕግ ከ 51% በላይ ድምጽ ካገኘ ያልፋል።

በሴነት ዉስጥ ተመሳሳይ ሂደት ቢኖርም ፊሊባስተር የሚሉት አሰራር አለ። አንድ ነጠላ ሴኔተር ዉይይቱ እንዲቀጥል በመጠየቅ ረቂቅ ሕጉ ላልተወሰነ ጊዜ ድምጽ እንዳይሰጥበት ማድረግ ይችላል። ነገር ግን ከመቶ ሴኔተሮች 60 ድምጽ ከተገኘ ረቂቅ ሕጎ ድምጽ እንዲሰጥበት ማስገደድ ይችላሉ። በሌላ አባባል ፊሊባስተሩን መስበር ማለት ነዉ። (እንግዲህ ይህንን ነበር ሴኔተር ኢንሆፍ ተጠቅሜ እንደ HR2003 አይነት ሕገ በሴኔት ዉስጥ ከቀረበ አግደዋለሁ ብለዉ ዝተዉ የነበሩት)

አንድ ረቂቅ ሕግ ከመሆኑ በፊት የሚከተሉት መሟላት አለባቸዉ።

- በሕዝብ ምክር ቤት ማለፍ አለበት (ሕገ መንግስቱን የሚያሻሽል ሕገ ከሆነ 2/3 ድምጽ ያስፈልጋል)
- በሴኔት ማለፍ አለበት(ሕገ መንግስቱን የሚያሻሽል ከሆነ 2/3 ድምጽ ያስፈልጋል)
- የሴኔትና የሕዝብ ምክር ቤቱ ረቂቅ ሕጎች የተለያዩ ከሆነ ከሁለቱም አካላት የተወጣጣ የጋራ ኮሚቴ ተመድቦ ለሁለቱም ተቀባይነት እንዲኖረዉ አድርጎ ሕጉን ያሻሽሉታል። (የማስታረቅ ስራ ማለት ነዉ)
- ከዚያም እንደገና ከጋራ ኮሚቴዉ የወጣዉ ሕግ ለሁለቱም አካላት ይቀርባል። ድምጽም ይሰጥበታል።
- በፕሬዘዳንቱ መፈረም አለበት( ፕሬዘዳንቱ ባይፈርምም በሴኔትና በሕዝብ ምክር ቤት ከ 2/3 ድምጽ በላይ ረቂቀ ሕጉ ካገኘ ሕጉ ያልፋል)
- ሕገ መንግስቱን የሚያሻሻል ሕግ ከሆነ (ከ50 ስቴቶች 34 ቱ ማጽደቅ አለባቸዉ)

## HR2003ን ለምን እንደምደግፍ

HR2003 የተሰኘዉ ሕግ ብዙዎቻችን እንዳሰብነዉ ሕግ ሆኖ ቢወጣ ኖሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ አድርገን የምናስብ በርካቶች ነን። በዚህም ምክንያት በአሜሪካ ምክር ቤት እንዲያልፍ ትልቅ ጥረት የተደረገዉ።

እኔም ይህን ሕግ እደግፈዋለሁ። የምደግፈዉ ግን በዉጭ አገር ያሉ ድህረገጾችና ፓልቶክ ክፍሎች እንደሚያወሩት ወያኔ/ኢሕአዴግን ተጠያቂ ስለሚያደርግ አይደለም። ቢሉን የምደግፈው በሌላ ምክንያት ነዉ።

HR2003 ሴነቱን አልፎ በፕሬዘዳንቱ ቢፈረምም፣ ወያኔ/ኢሕአዴግ ከሕግ አስፈጻሚዉ አካል ጋር አብሮ እስከሰራ ድረስ አንዳች ለዉጥ ሊያመጣ አይችልም ባይ ነኝ። ሕጉ የኢትዮጵያ መንግስት እንዲፈጽማቸዉ ያስቀመጣቸዉ መመዘኛዎች አሉ። እነዚህ መመዘኛዎች ካልተሟሉ አንዳንድ እርምጃዎች በኢሕአዴግ ላይ እንዲወሰዱ ይጠይቃል። ከነዚህ እርምጃዎች መካከል አንዳንድ (ለጸረ ሽብርተኛዉ ጦርነት፣ ለሰላም አስጠባቂዉ ኃይል ፣ ከደህንነት ጋር ለተገናኙ ጉዳዮች፣ ለመሰረታዊ የሰብዓዊ እርዳታዎች ..የመሳሰሉት ሳይጨምር) ሌሎች እርዳታዎች ለመንግስት እንዳይሰጥ ያግዳል።።

እንግዲህ አስቡት የስቴዲፓርተመንት ሰዎች ከፊለጉ በኢትዮጵያ እየታዩ ያሉ ዉጫዊ ለዉጦችን እያሳዩ የኢትዮጵያ መንግስት በHR2003 የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች እያሟላ ነዉ ብለዉ በቢሉ የተጻፉ «ቅጣቶችን" ተግብራዊ እንዳይሆኑ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ከዚህም ደግሞ ትንሽ አልፈን እንሂድ። እንበል የኢትዮጵያ መንግስት በይፋ የሰብዓዊ ሙብት ረገጣዉን ቢቀጥልና መመዘኛዎችን እንደጠበቀ አድርገዉ ማሳመን ካልቻሉ ለኢሕአዴግ ይሰጡ የነበሩ እርዳታዎችን ለደህንነት ወይም ለጸረ-ሽብርትኝነት ትግል ያስፈልጋል ብለዉ በአንዱ በኩል የተከለከለዉን ገንዘብ በሌላ መልኩ ሊሰጧቸዉ ይችላሉ።

ይህ ብቻ አይደለም። የHR2003 ረቂቅ ሕግ በማጠቃለያዉ ላይ ያሰፈረዉ ብዙ የማይታይ አብይ አንቀጽ አለ። የሕግ አስፈጻሚዉ አካል የአሜሪካን ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ ሕጉ ተግባራዊ እንዳይሆን ማድረግ ይችላል ይላል። (waive ሊደረግ ይችላል) በሌላ አባባል፣ ሕጉ በአሜሪካን ምክር ቤት እንዳለፈ ሁሉ በሴኔት አልፎ በፕሬዘዳንቱ ቢፈረምም ፕሬዘዳንቱ ከፈለገ «አይ የኢትዮጵያ መንግስት ወዳጃችን ነዉ። እነርሱን መጫን የለብንም» ብሎ የተደከመበትንና የተለፋበትን ሕግ ሊያቆመዉ ይችላል ማለት ነዉ።

ሰዉ የገደሉ ባለሥልጣናትም ቪዛ እንዲከለከሉ HR2003 ይደነግጋል። ይህ በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ነዉ። እንድ ሰዉ ቪዛ እንዲከለከል ወንጀለኛ የተባሉ ሰዎችን ስም ዝርዝር የአሜሪካ ኤምባሲ ሊኖረዉ ይገባል። ይህን የስም ዝርዝር ለማግኘት ሰዎች መጀመሪያ በፍርድ ቤት ተከሰዉ «ጥፋተኛ» መባል አለባቸዉ። ጥፋተኞችን ለፍርድ የሚያቀርብ የሕግ ሥርዓት በሌለበት ሆኔታ ደግሞ ጥፋተኛ የሚባልና ቪዛ ሊከለከል የሚችል ማንም ባለስልጣን ሊኖር አይችልም።

ስለዚህ ሕጉ እንደተወራዉ ጥርስ ያለዉና ትልቅ ለዉጥ በአንዴ ሊያመጣ የሚችል ሕግ አይደለም። በዚህ አንጻር ከመጠን ባለፈ የHR2003ን ጥቅም በመለጠጥ ሕዝባችን ብዙ ያሞኘነዉና ያታለልነዉ ይመስለኛል።

«ታዲያ ለምንድ ነዉ ወያኔ/ኢሕአዴግ HR2003ን የሚቃወመዉ ?» የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ/ኢሕአዴግ ስለተቃወመዉ አንድ ነገር ሁልጊዜ ጥሩ ነዉ ማለት አይደለም። ምናልባት አዉቀዉ እኛ በዚያ ላይ ጊዚያችንን እንድናጠፋ ጩኸት ሊያሰሙ ይችላሉ። በሁለተኛ ደረጃ ወያኔ/ኢሕአዴግ HR2003ን በርግጥ ቢቃወምም የሚቃወምበት በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል ብዬ የማስበዉ አለ። ይህ ወያኔ/ኢሕአዴግ የሚቃወምበት የሚመስለኝ ምክንያት እኔ ቢሉን የምደግፍበት ምክንያት ነዉ።

HR2003ን የምደግፈዉ ለዲሞክራሲ ግንባታ  ገንዘብ ስለመደበ ነዉ። ይህ ገንዘብ ሲቪክ ማህበራት በኢትዮጵያ እንዲስፋፉ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች በገንዘብ እጦት ችግር እንዳያጋጥማቸዉ ሊረዳና ትልቅ አስተዋጾ ሊያደርግ የሚችል ገንዘብ ነዉ። ጋዜጦች እንዲበዙ ማድረግ ይቻላል። በየክልሉ የህዝቡን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማጎልበት የተለያዩ ሴሚናሮችን ዎርክሾፖችን ማዘጋጀት ይቻላል። ኢትዮጵያዉያን ሙብታቸዉን አይተዉ በተለያዩ የሞያ ማህበራት እንዲደራጁና ለሙብታቸዉ መከበር እንዲቆሙ ማንቃት ይቻላል። ገንዘብ ትልቅ ሚና ይጫወታልና።

ኢሕአዴግ አንዱ መሳሪያዉ ሲቪክ ማህበራትን መቆጣጣር ወይንም ደካማ እንዲሆኑ ማድረግ ነዉ። የሚያደክማቸዉም ትልቁ መሳሪያ በገንዘብ ችግር እንዳይላወሱ እያደረጋቸዉ ሲሆን እንደዚያም አድርጎ ካልቻለ ወደ ማስፈራራት ከዚያም ወደ ማሰር ይደርሳል። ሲቪክ ማህበራት ከተደራጁ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ አቅም ካላቸዉ፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ እንዲተማመን ከተደረገ ትልቅ ለዉጥ ሊመጣ እንደሚችል ምርጫ 97 አሳይቶታል። ስለዚህም በተቻለ አቅም ህዝብ እንዳይደራጅ ማድረግ ወያኔ/ኢሕአድግ ለስልጣኑ መቀየት ቁልፍ አደርጎ ነው የሚያየዉ። HR2003ን የምደግፍበት ኢሕአዴግም የሚቃወምበት ምክንያት እንግዲህ ይህ ይመስለኛል።

## ለHR2003 አለማለፍ ኢንሆፍ ተጠይቂ አይደሉም !

HR2003 ፣ ከሁለት አመታት ትግል በኋላ በሕዝብ ምክር ቤት ዉስጥ ሊያልፍ ችሏል። HR2003 ሊያልፍ ጥቂት ሳምንታት ሲቀሩት የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች መፈታታቸዉ ይታወሳል። የሚቀጥለዉ ደረጃ ተመሳሳይ ሕግ በሴኔት እንዲቀርብ ማድረግ ነበር። ይህን ሊያደርግ የሚገባዉ በሴኔት የዉጭ ግንኙነት ኮሚቴ የአፍሪካ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ ነበር። ነገር ግን ንኡስ ኮሚቴዉ እስከአሁን ድረስ ምንም አይነት ኢትዮጵያን የሚመለከት ሕግ በሴነት ዉስጥ አላቀረበም።

እዚህ ላይ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ዘንድ እየተፈጠረ ያለ ሌላ ትልቅ ውዝንብር አለ። ለHR2003 አለመንቀሳቀስ ሴኔተር ኢንሆፍን ተጠያቂ የማድረግ ነገር ይታያል። ነገር ግን እዉነታዉ ከዚህ የራቀ ነዉ። ሴኔተር ኢንሆፍ HR2003ን እንዳያልፍ አላደረጉም። ምንም አይነት ፊሊባስተርም አልተጠቀሙም። ፊሊባስተር ለማደረግ መጀመሪያ ረቂቅ ሕጉ መኖር ወይንም፣ በሴኔት መቅረብ አለበት። የሌለ ነገር ላይ ፊሊባስተር አይደረገም። እርግጥ ነዉ ሴኔተር ኢንሆፍ ኢትዮጵያን በተመለከተ የተናገሩት አንዳንድ አሳዛኝ አባባሎች አሉ። ለዚያም እንወቅሳቸዋለን፣ እናወግዛቸዋለንም። ነገር ግን ገና ባላደረጉት ነገር ላይ መከሰስ የለባቸዉም። መቼም እዉነትን ይዘን በእዉነት ላይ ብንመሰረት ጥሩ ይሆናል ብዬ አስባለሁኝ።

እንበል HR2003 በሴኔት ዉስጥ ቢቀርብ፣ ሴኔተር ኢንሆፍ ፊሊባስተር ቢያደርጉትም ኖሮ፣ ኢንፎፍ በጣም የማይወደዱ ሴኔተር ስለሆኑ በቀላሉ እርሳቸዉን የሚገለብጥ ከ 60 በላይ ድምጽ ማግኘት ይቻል ነበር። (ኢንሆፍ በአቡ ግሬብ እሥር ቤት በአንዳንድ የአሜሪካ ወታደሮች የተሰራዉን ግፍ እንኳን ያላወገዙ አሳዛኝ ሰዉዬ ናቸዉ)

## የሴኔት ዴሞክራቶች ለምን HR2003ን ለማቅረብ አልቻለም?

በሴኔት የዶናል ፔን አይነት ሚና ያላቸዉና የዊስኮንሲኑ ዴሞክራቲክ ሴኔተር የሆኑት ራስ ፋይንጎልድ ናቸዉ። ሴኔተር ፋይንጎልድ ኢትዮጵያ ዉስጥ እየተደረገ ያለዉን የሰብዓዊ መብት ረገጣ ጠንቅቀዉ የሚያዉቁ፣ ይህንንም በተመለከተ ብዙ ጊዜ በንግግር ያወገዙ ሰዉ ናቸዉ። የቅንጅት መሪዎች በታሰሩ ጊዜና በኦጋዴን ከፍተኛ እልቂት ሲፈጠር ከአሥር በላይ ሌሎች ሴኔተሮችን አስተባበረዉ የጋራ መግለጫ ያወጡ ጠንካራና የሚደነቁ ሴነተር ናቸዉ። የኢትዮጵያ መንግስት ወታደሮችን በሶማሊያ ከማስገባቱ በፊትም በአዲስ አበባ አቶ መለስ ዜናዊን ባናገሩ ጊዜ ኢትዮጵያ ጥንቃቄ እንድትወስድና አጥብቃ እንድታስብበት የመከሩ ሰዉ ናቸዉ። « ጦርነቱን ልታሸንፉ ትችሉ ይሆናል። ሰላሙን ግን ማሸነፍ በጣም ይከብዳል» ነበር ያሉት። (ሰላም ማሸነፍ ሲሉ ሰላምን እንዲኖር የሚደረገዉ ትግል ማሸነፍ ማለታቸዉ ነዉ - win the peace)

በአሜሪካ ሴኔት ዉስጥም የሰብዓዊ መብትን መከበር በተመለከተ የማያሻማና በመርህ ላይ የተመሰረተ አቋም መያዛቸዉ ብዙ አድናቂ አትርፎላቸዋል። ፕሬዘዳንት ቡሽ ፍርድ ቤትን ሳያስፈቅዱ የዜጎች ስልክ እንዲጠለፉ ባደረጉ ጊዜ በቀዳሚነት «የዜጎች መብት ተጥሷል ፣ ፕሬዘዳንቱ ሕግ ጥሷል» ብለዉ የተከራከሩ በጣም ከማከብራቸዉ ጥቂት ቆራጥ ሴኔተሮች ዉስጥ አንዱ ናቸዉ።

ታዲያ እኚህ ሰዉ ለምንድን ነዉ HR2003ን እንዳለ ወስደዉት ወይንም ደግሞ የራሳቸዉን አርቅቀዉ አሁን ባለዉ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ተጽኖ እንዲደረግ ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆኑት ? የሚል ጥይቄ ሊነሳ ይችላል። «ለሰብዓዊ መብት ግድ ስለሌላቸዉ ነዉ» ብዬ ለማለት ይከብደኛል። እኔ እንደሚመስለኝ ኢትዮጵያ በአካባቢዋ ካሉ አገሮች አንጻር ስትታይ እጅጉን የተሻለች በመሆኗና ያሉባትን ችግሮች በስቴት ዲፓርተመንት በኩል ግፊት ማድረጉ ይሻላል በሚል ምክንያት ሳይሆን አይቀረም ሴኔት ዴሞክራቶች ብዙም ወያኔ/ኢሕአዴግን መጫን ያልፈለጉት። እያስፈራሩ ግፊት ከማድረግ በማሳመን አቋምን ማስለወጡን የመረጡ ይመስላል።

## የHR2003 እና ሌሎች የዲፕሎማቲክ ሥራዎች ከአሁን በኋላ

እስከ ሕዳር 2001 ድረስ ሴኔት ዉስጥ ቀርቦ በፕሬዘዳንቱ ካልተፈረመ HR2003 ይሞታል። ከጥር 2001 በኋላ አዲስ ምክር ቤት ነዉ የሚኖረዉ። እንደገና «ሀ» ተብሎ የሕዝብ ምክር ቤት እንዲያልፍ መደረግ ይኖርበታል

ማለት ነዉ"። ስለዚህ የHR2003 ጉዳይ በትልቅ ጥይቄ ዉስጥ የሚገባ ነዉ። ስለሆነም እንቅስቃሲያችን ከHR2003 ባለፈ መልኩ ማጧጧፍ ይጠበቅብናል። ለዚህም እንዲረዳ የሚከተሉትን ሃሳቦች አቀርባለሁኝ።

- ኢትዮጵያዉያን ከሴኔተሮችና ከምክር ቤት አባላት ጋር የምናደርገዉን ዉይይት መቀጥል አለብን። እነዚህን የሕዝብ ተወካዮች ችግር ሲፈጠር ብቻ አይደለም ቢሯቸዉን ማጣበብ ያለብን። በየጊዜዉ ያለዉን ሁኔታ ብናሳዉቃቸዉ የበለጠ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የጠለቀ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ማድረግ እንችላለን።

- እዉነተኞች መሆን መቻል አለበን። እኛ ይህን አገዛዝ እንጠላዉ ይሆናል። እነርሱ ግን እኛ በምናየዉ አይን አይደለም የሚያዩት። ግልጽ መረጃ ይፈልጋሉ።

- ጠንካራ አቋም ለመዉሰድ ጊዜ ይፈጅባቸዋል። ትእግስት ሊኖረን ይገባል።

- ለእርቅና ለሰላም የበለጠ ትኩረት ይሰጣሉ። ኢሕአድግን በነርሱ ፊት እንደጠላት አድርጎ ማየት ጉዳት አለዉ። ለኢሕአዴግ ጀርባ እንዲሰጡ ካስፈለገ አማራጮችን በግልጽ ማሳየት አለብን። እኛ ሰላም ወዳድ ፣ ሁሉን አቀፍ የሆንንና የሞራል ከፍተኛዉን ቦታ (moral high ground) የያዝን መሆናችንን ማሳየት አለብን።

- መሰረት ለሌለዉ ወገዛና ክስ ቦታ አይሰጡትም። ጭቅጭቅ ወይንም ጥል (confrontational approach) አይፈልጉም። ኢሕአዴግ ቢወገድ ማን ነዉ ሕግና ስርዓት የሚያስጠብቀዉ ? ማነዉ ኢሕአዴግን ተክቶ ኢትዮጵያን አረጋግቶ ሊመራ የሚችለዉ ? ለሚሉና ለመሳሰሉ ጥያቄዎችን መመለስ መቻል አለብን።

- በሁለት ወይንም በሶስት ግለሰቦች የሚመራ ሳይሆን፣ በርግጥ የተቀናጀ በዉጭ የሚኖሩ በዉጭ ግንኙነት ጉዳይ ላይ ልምዱ ያላቸዉን አስተዋይ ኢትዮጵያዉያንን አሰባስቦ፣ የሲቪክ ማህበራትንና የፖለቲካ ድርጅቶችን በአንድ ላይ አምጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ሁሉም በፊናዉ የሚያደርገዉ ሩጫ ወይንም ሶስት ግለሰቦች መግለጫ በማዉጣት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዉጤት አላመጣም። አያመጣምም።

- የአሜሪካን ኮንግረስን የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል አጋር ለማድረግ እንደምንሞክረዉ ሁሉ የሕግ አስፈጻሚውን አካልም ወደኛ ለመሳብ መታገል አለብን። የሕግ አዉጪዉ አካል (የአሜሪካን አምባሳደር፣ ዶ/ር ጄንዳዪ ፍሬዘር ...) ዛሬ እኛን ላይደግፉ ይችላሉ። ከጎበዝን ነጋ ወደ እኛ ልናመጣቸዉ እንችላለን። ዛሬ አቶ መለስን ስለደገፉ መሳደብና በነርሱ ላይ አሉታዊ የሆኑ ጽህፎችን ማቅረብ አይጠቅምም። እኛ አሁን የሚያስፈልገን ወዳጆች እንጂ ጠላቶች አይደለም። (አላወቅንም እንጂ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ አቶ መለስ ከዶናልድ ፔን ይልቅ ለዶ/ር ጄንዳዪ ፍሬዘር ነዉ ትልቅ ቦታ የሚሰጡት። )

እንግዲህ HR2003 ሕግ ሆኖ ባለማለፉ ተጠያቂ ማድረግ ያለብን ሴኔተር ኢንሆፍን ወይን በሴኔት ያሉ ዴሞክራቲክ ሴኔተሮችን ወይንም ዲኤልኤ ፓይፐርን ሳይሆን እኛኑ እራሳችንን ነዉ። በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዉያን፣ ከዉጭ አገር ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉን ትግል ለመምራት ከመሞከር ወይንም ኢትዮጵያ ዉስጥ ሆነዉ እየታገሉ ያሉትን እንዲህ አድርጉ እንደዚያ አታድርጉ ከማለት ይልቅ፣ በዉጭ የምንሰራዉ የዲፕሎማቲክ ሥራ ላይ ማተኮር ይጠበቅብናል። ቆም ብለን፤ ካለፈዉ ተምረን፣ ከዚህ በፊት ካደረግነዉ በተለየ መልኩ የዲፖሎማሲዉን ሥራ መስራት አለበን። ባራክ ኦባማ እንዳሉት አንድ ነገር ደግመን ደጋግመን በተመሳሳይ መልኩ እያደረግን የተለየ ዉጤት መጠበቅ የለብንም።፡